# የምፅዓቱ የምሥራች



ቅጽ 80 ቁጥር
11(12፤81)ቁጥር ()961

“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ወደ እኔ ጩኹ እኔም እመልስልሃለሁ”

ትንቢተ ኤርሚያስ 33:3

## እግዚአብሔርን ስለመገናኘት

(በሄንሪ ብላክቤይና ሊዮናርድ ራቪንሂል)

ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር በተገናኘበት ወቅት ታላቅ የእግዚአብሔር ገብኝት ማግኘቱን ቅዱስ መፅሐፍ ያስተምረናል ሳምሶንም እንደዚሁ የእግዚአብሔር መንፈስ በተገናኘው ጊዜ ትልቅ ታምራት በህይወቱና በሀገሩ ላይ ደርሷል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ መልዕክቱን በቤተመቅደስ ተገኝቶ ባሰማበት ወቅት የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው በሚል የቃሉ ንባብና በቅዱስ መንፈስ ብርቱ አፅናኝነቱን በህይወቱና በአገልግሎቱ መስክሯል። በሐዋሪያቱም ላይ ቅዱስ መንፈስ በወረደበት ጊዜ እጅግ ልዩ የሆነ ገብኝትና የነፍሳት መዳን ተከስቷል።

የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ በጎይል ወረደ (መሳፍንት 14:6) ‹‹የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው›› (ሉቃስ 4:19) ‹‹ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል›› (ሐዋርያት 5:29)

በዚህ ወቅት ስርዓትን ብቻ የተከተለ መንፈሳዊ ስብሰባ ለሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ ለመላው አለም መፍትሔ ያላስገኘ በመሆኑ እግዚአብሔርን በብርቱ የያም ፀሎት ምልጃ መገናኘት የሁሉም ክርስቲያን መብት፣ ግዴታ እና ሃላፊነት ነው። ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር በሚጋጩ ሀገሮች መንግስታት ጥፋት እልቂት፣ እርኩሰትና ጥፋት የተሞላበት ሆነዋል።

ከእግዚአብሔር የተለዩ መንግስታትና የሀገር መሪዎች በታሪክ የተፃፈውና በህይወታችንም ያየነው እንደሚመሰክረው ክፋታቸውን አይተናል፤አንብበናል፤ እያለፍንበትም ነው። እግዚአብሔር ዓለምና መላዋን የሚቆጣጠር የፈጠርና በፈለገው ጊዜ የሚያነቃንቅ የሚያነሳና ከፈለገም የሚያፈርስና የሚታደግ ነው።

እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ ሕዝቦቹን የፈጠረ የባረክ የሚታደግ እንደአስፈላጊነቱም ለበጎ የሚቀጣ የሚያስተካክል በመጨረሻም በእምቢታ የቀጠሉትን የሚያጠፋ አምላክ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምራል።

“የማይገዛ ሕዝብና መንግስት ይጠፋል፣ እነዚያ አሕዛብም ፈፅመው ይጠፋሉ” (ኢሳ. 60፡12)

የግብፁ ፈርኦን አገዛዝን ለማስወገድ እግዚአብሔር ተከታታይ አስር መቅሰፍቶችን ልኮበታል። በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማሳደድ ላይ ሳለ በቀይ ባህር ሰጥሞ ቀርቷል። (ዘፀዓት 12)

በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ ክፋትን፣ እልቂትን ጥላቻና ዘረኝነትን የሚዘራው ክፉው ሰይጣን ነው። ሰይጣን ሰዎች የተሰጣቸውን የእግዚአብሔር ጥበብና የመንቃት ችሎታ የሚያጡበት የእንቅልፍ ሕይወት ላይ ክፉ ዘሩን ይዘራል። ያም ክፉ ዘር አድጎ ፍሬው የሚጎዳ ይሆናል” ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ (ማቴ. 13፡25)

በብዙ ሀገሮች ታሪክ እንደታየው ክፍተኛ የዘር ማጥፋት እልቂት የሚፈፀመው በሰዎች መካከል የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ከተዘራ በኋላ በዚያ ፕሮፓጋንዳ በተሞሉ ሰዎች እጅግ ዘግናኝ ወንጀሎች በሰዎች ላይ ለመፈፀመ የሀገራችን የቅርብ ጊዜ ትዝታዎች የሩዋንዳና የሶሪያን የቀደመ የዓለም የዘር ማጥፋት ታሪኮች ይመሰክራሉ።

በተለይ ብዙ ሕዝብ በሚከማችባቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስብሰባዎችና ሥነጽሁፎች ላይ ይህን መሳይ ክፉ አጥፊ ዘር እንዳይዘራና እንዳይስፋፋ የሰዎች ደህንነት የሚሰማን የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ልንጠነቀቅ ልንፀልይና ልንገስፅ ልንመክርም ያስፈልጋል።

ባለንበት ዘመን የኃጢያት የእርኩሰት ዕዋ ሞልቶ በመፍሰስ ላይ በመሆኑ ህሊና ያለው ሁሉ ይገነዘበዋል። ይህን ለመታደግ ለማስተካከል ክርስቲያኑ ማህበረሰብ የበለጠ ኃላፊነት ያለው አይኖርም።

በዓለማችን ከዚህ በፊት ከታዩት ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ዋዜማ በፊት ከታዩት አሳሳቢ ሁኔታዎች በባሰ መልኩ ምልክቶች እየታዩ ናቸው።

ሊመጣ ካለው ጥፋት መልዕክተኛ የሆነቸው ቅድስት ቤተክርስቲያን የአማኞች ማህበረሰብ በሚያሳዝን ሁኔታ ራሷንም ከጥፋቱ ከእርኩሰቱ ከመለያየቱ ማዳን በማትችልበት ሁኔታ ላይ እንዳለች ቅን መንፈስ ያለው ሁሉ ይረዳዋል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር በየዘመናቱ ሊመጡ ያሉትን ጥፋቶች ክፋቶች ሕዝቡ ተረድቶ ይመክት ዘንድ በነብያቱ በሐዋርያቱ በደቀመዛሙርቱ በኩል ወቅታዊ መልዕክቱን ከማስተላለፍ የተቆጠበበት ጊዜ የለም። (ትንቢተ ደንኤል 5፡26፤ ዘፍጥረት 41፣ ኢሳ. 10፡5)

የእግዚአብሔር ህዝብ በመተላለፉ ምክንያት ለስደት ለስቃይና ለሰቆቃ ይዳረጋል። ይህም ለመስተካከል ለመመለስና እግዚአብሔርን

ለመፈለግ እንዲረዳው እግዚአብሔር እራሱ የሚያዘጋጀው ሥርዓት ነው።

የእግዚአብሔር ሕዝብ በሰው ምድር በባዕድ ሀገር በተሰደደበት ወቅት ትውልድ ሀገሩን እንደሚያስብ የእስራኤል ታሪክ የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነው ምስክር ነው። በአዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነው ደግሞ የተወለደው ክርስቲያኑ ማህበረሰብ በመተላለፉ ከእግዚአብሔር ሕዝብነት ውጪ ሲሆን ይህ ሁኔታ ትካዜ ይመጣበታል።

"የእግዚአብሔርን ዝማሬ በባዕድ ምድር እንዴት እንዘምራለን" (መዝ. 136፡4)

ብዙ ሰዎች ሀገሮችና መንግስታት ከገቡባቸው ችግሮች ለመውጣት የሰው መፍትሄ ሲፈልጉ ይገኛሉ፡ ይህ ግን ምንም መፍትሄ አያስገኝም። የእግዚአብሔር መፍትሄ ግን በቅዱስ መንፈሱ አስተማማኝና ዋስትና ያለው ነው። ለችግሮቻችን ለመከራችን ወደ ጌታ እንጩህ አርሱም ይመልስልናል።(ዘካ. 4፡6፣ ኢሳ. 10፡27፣ ኤር. 33፡3)

## መልዕክት ከአሳታሚው (ሪች ካርማይክል)

## ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ይቀርባችኋል

የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ በአምሳሉ የተፈጠረው የሰው ዘር እርሱን እንዲመስልና እንዲቀርበው ነው። ከመጀመሪያው የቅዱስ መፅሐፍ ክፍል እስከ መጨረሻው ድረስ እግዚአብሔር የፈጠረው ሕዝብ ከእርሱ ጋር አንድ እንዲሆን በማቀድ የተሞላው የእግዚአብሔር ሀሳብ ነው። (ዘፍ. 3፡8፣ ራዕ. 21፡3)

እግዚአብሔር የፈጠረውን የሰው ዘር ሊመዘን በማይቻል ፍቅር ይወደዋል፤ ይንከባከበዋል። ከዚህ ፍቅርና ክብካቤ የተነሳ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ፍፁም የተሟላ ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል።(ማር. 12፡30)

የምጽዓቱ የምስራች ዓለም አቀፍ የወንጌል አገልግሎት አንባቢዎች ሁሉ የዚህ መሰሉ ፍቅርና ግንኙነት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራቸው ዘንድ ይጸልያል፣ ይመኛል፤ በትጋትም ይሰራል።

ይህን የምታነቡ ሁሉ ይህ መልካም ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ከሌላችሁ ዛሬ የምንሰጣችሁ የእግዚአብሔር መልዕክት ሮሜ 2፡4 ነው።

በተጨማሪም ወደ ዕብራውያን መልዕክት 4፡7፣ ዘዳግም 4፡29 በሚናገረው መሰረት ልባችሁ ደንዳና በማድረግ ከእግዚአብሔር ህብረት ግንኙነትና ዘለዓለማዊ ፍቅር እንዳትርቁ ነው።

## ጌታን ስለመጠበቅ

እግዚአብሔርን በትዕግስት ስለመጠበቅ የሚያስተምሩን የእግዚአብሔር ሰዎች ንጉስ ዳዊትና ኢዮብ ናቸው።

ዳዊትና ኢዮብ በደረሰባቸው ክፉ ጉዳት ሳይታቀቡ ጌታን እንደጠበቁት እኛም እንጠብቀው።(መዝ. 27:4፣63:1፣ኢዮብ 1:22)

## እግዚአብሔር ቀርቦን ሳለ

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በአምሳሉ ከፈጠረው ጊዜ ጀምሮ ሊቀርበው ይፈልጋል። ከጠፋበት ወዴት ነህ ብሎ መልሶታልም።

በዚህ አዲስ ዘመን ጅማሬ ጌታ እንድንቀርበው ይፈልጋል። በቃሉና በፀሎት እንቅረበው። ሌሎችም እንዲቀርቡት ፀሎትና ምልጃ እናድርግ። (ያዕ. 4:8)

## ተሀድሶና መነቃቃት በጨለመበት ሰዓት ይመጣል

ገናና ሆኖ የተገነባው የዓለማችን ሥልጣኔና ጥበብ እንዳይፈርስ ስጋቱ በመጨመር ላይ ይገኛል። በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ እርኩሰቱ፣ ክፋቱ፣ ምዝበራውና ዘረኝነቱ በአሳፋሪ ሁኔታ በመስፋፋት ላይ ነው።

ይህ ወቅት ምን ያህል እንደጨለመ የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ነግሮናል፣ አስጠንቅቆናል። መውጫውንም ለእኛ ለልጆቹ አመላክቶናል። (ኢሳ. 64:7፣ ፊሊ.. 3:7፣ ማር. 11:22)

እግዚአብሔር እኛ አማኝ ልጆቹን ከምንኖርበት ዓለም (ሥፍራ) እንድንርቅ ለሚፈጠሩ ችግሮች ዝምታን እንድናሳይ አላዘዘንም። ይልቁንም ለመፍትሄው እንድንፀልይ እንድንተጋ ያሳስበናል። "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፣ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም" (ማቴ. 5:14፣ ማር. 6:7)

በዓለማችን ላይ እውነተኛው ብርሃን በኃጢያትና በክፋት ጨለማ ያሉትን ወደ ቀናው መንገድ የሚመልሰው የጌታ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል።

ይህንን ብርሃን ክርስቶስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ካለው ጌታ ያገኘን ሁሉ ለሌሎች ማስተላለፍና በጥንቃቄ መጠበቅ አለብን። "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ" (ማቴ. 5:13)

ጨው በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገሮች ለምግብ ማጣፈጫነት ከሁሉም በላይ ስጋና የመሳሰሉት ምግቦች እንዳይበላሹ የሚረዳ ጠቃሚ ነገር ነው።

እንደዚሁም ሁሉ ክርስቲያኖች በስነ ምግባር በሥራና በንግግር የተበላሸ ማህበረሰብን እንደ ጨው ውስጡ በመግባት ከብልሽት የሚያተርፉ ናቸው። ዛሬ ክርስቲያኖች ላሉበት ማህበረሰብና ሀገር ብልሽት እንደ

ጨው ገብተው ካልፈወሱ እንደድንጋይ መጣላቸው አይቀርም፣ እያየንም ነው።

እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ እንደተናገረው በዚህ በጨለመው ጊዜ ተሃድሶን በቤተክርስቲያኑ በማህበረ ምዕመናን በክርስቲያኖች ቃልና ህይወት ምስክርነት ያመጣል።

# በእግዚአብሔር ዙፋን ስር የሚገኝ ብርታት

## በቻርለስ ስፐርጂን (የስብከት ልዑል)

በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ፀሎት ትልቅ ሥፍራ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ለማንኛውም ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴና የክርስቲያኖች ህይወት ስኬት ፀሎት ዋነኛ ተፈላጊ ጉዳይ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በፀሎት እንድንተጋ እንድንቃትትና እንድንሰማራ ዘወትር ያሳስበናል። ፀሎትን ከሚያስወግድ ኃጢአት እንድንጠበቅ ንስሃም እንድንገባ ያሳስበናል።

በፀሎት መንፈስ ብቻ ስንሆን ሁሉን ማድረግ ወደሚችለው በሁሉ ላይ ስልጣን ባለው እግዚአብሔር ፊት እንገኛለን። "በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ፀጋ እንድንቀበል ወደ ፀጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" (ዕብ. 4፡16)

ወደ ሀገር መሪ ቤት ወይም ቤተመንግስት ተጠርተን ስንገባ ብዙ ክብካቤ ምህረትና መስተንግዶ እንደሚጠብቀን ሁሉ የምድርና መላዋ ፈጣሪ ጌታ ዙፋን ስር በፀሎትና በቃሉ ስንቀርብ የሚጠቅመንን የሚባርከንን ምህረትና ፀጋውን እናገኛለን። እግዚአብሔር የሚያስጨንቀንን ሁሉ ለእርሱ እንድንተውለት በሰጠን የተስፋ ቃሉ መሰረት ለእግዚአብሔር መሻታችንን የምናቀርበው በዙፋኑ ሥር በፀሎትና በምልጃ ስንገኝ ነው። (1 ጴጥ. 5፡7)

እግዚአብሔር ቅን ደግ ፈራጅ ሲሆን ከእግዚአብሔር የፍቅር ባህርይ የተነሳ እኛ አማኝ ልጆቹ የእግዚአብሔር ባህርይ የሆነውን ፍቅሩን የምናገኘው በዙፋኑ ሥር በመውደቅ ነው። (1 ዮሐ. 4፡18)

እግዚአብሔር ቀንና ሁኔታ አይቶ የማይጥለን የማይተወን በዙፋኑ ላይ ፀንቶ የሚኖር ማንም ሊነቀንቀው የማይችል ሁሉን ቻይ አምላክ በመሆኑ ነው።(ዕብ. 13፡5)

ሰዎች ወደሚተማመኑበት ሰው በድፍረት በመሄድ የሚፈልጉትን ነገር እንደሚጠይቁ ሁሉ እኛ አማኞች ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በፀሎት በድፍረት እንቅረብ። አሜን!

# እግዚአብሔርን ለሀገር ጉዳዮች እንገናኘው

በእግዚአብሔር ፊት ስንሆን በኑሮ መሰረታዊ ለውጥ እናገኛለን። የሰው ልጅ ባህሪይ ከልጅነት እስከ ሽምግልና በለውጥ ሂደት የተሞላ ነው። ለውጥ በጎና ክፉ ጎኖች ሲኖሩት በጎ ጎኖችን ለማግኘት ብዙ ጊዜ ሰዎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያካሂዱ ኖረዋል፤ ዛሬም በማካሄድ ላይ ናቸው።

ለሰው ዘር በጎ ለውጦች የተገኙት በእግዚአብሔር ሰዎች ትጋት በቅዱስ ቃሉና በቅዱስ መንፈሱ ምሪት ለመሆኑ በታሪክ ሁሉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። (ዕብ. 4፡12)

ነብዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በተገናኘበት ወቅት ከእግዚአብሔር ኃያልነት የተነሳ ጠፋሁኝ በማለት የእርሱንም የወገኖቹንም ርኩሰት በመናዘዝ ታላቅ የእግዚአብሔር የጉብኝት መልዕክት ሊቀበል በቅቷል። "ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሰራዊተ ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ አልሁ" (ኢሳ. 6፡5)

በዚህ ወቅት ኢትዮጵያችንም ሆነ መላው ዓለም በአሳዛኝ ሁኔታ በመራመድ ላይ ናቸው። ለዚህ የከፋ ሁኔታም ትልቅ መፍትሄ ሊያመላክቱ የሚችሉት ክርስቲያን ወገኖች ናቸው።

አንድ ሰው ብቻ እንኳን ቢሆን በትክክል የእግዚአብሔርን ቃልና መንፈስ የተከተለ ለሀገርና ለዓለም በጎ ለውጥ ካለንበት ውጥንቅጥ መፍትሄ ሊያሳይ ሊረዳ ይችላል። ሙሴ አንድ ሰው ሆኖ ከቤተመንግስት የልጅነት መብት ይልቅ በባርነት ያሉት ወገኖቹ ስቃይ በልጦበት ለሕዝቡ ነፃነትና መሻሻል ምክንያት ሆኖ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ሆነ።

ሙሴ በእግዚአብሔር በተጠራበት ወቅት ብቃት እንደሌለው ቢናገርም እግዚአብሔር አበርትቶት ኢያሱን የመሰለ ምክትል ዮቶርን መሳይ ተባባሪ በማግኘት ህዝቡን ለነፃነት ያበቃው ምሳሌ ይሁነን።

# እግዚአብሔርን በቃሉ መገናኘት

## የእግዚአብሔርን ቃል እንረዳው (በቶዘር)

የእግዚአብሔር ኃይል መሰረቱ ቅዱስ ቃሉ ነው። መፅሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን የሚተካ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ሙላት የሚያደርስ የእግዚአብሔር ትልቅ በረከት ነው። መፅሐፍ ቅዱስን አንብበን

እግዚአብሔርን ካልተገናኘን በትክክል መዕሐፍ ቅዱሱን አላነበብነውም።

መዕሐፍ ቅዱስ ስለዘመናችን የሚናገር ሲሆን በየዘመኑ የሚከሰቱ ኃጢያቶችን የሚወቅስ ወደ ቅድስና የሚመልስ የእግዚአብሔር ትልቅ መሳሪያ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን የሚቆጣጠርና የሚመራ ሲሆን የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ቅዱስ መዕሐፍ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያሳድግና በትክክለኛ መንገድ እንድንጓዝ የሚመራ ነው።

በእግዚአብሔር ቃል በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱ ቃሎች ሰዎችና ድርጊቶች ሁሉ ለክርስቲያኖች ሕይወትና ንግግር ምሳሌና መመሪያ ይሆኑ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቅዱሳን የእግዚአብሔር ሰዎች የጻፉልን ነው።

## ዘመናችንን እንመርምር

ዘመናችንን እንዴት እንመርምር? በዚህ ወቅት ዘመናችን ተሃድሶና መንፈሳዊ መነቃቃት እጅት የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። ይህ ጊዜያችን በቅዱስ መዕሐፉ የተጻፉት ትንቢቶች ሁሉ በአብዛኛው የተፈፀመበት ወቅት ነው። አያሌ መዕሐፍትም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተጻፉልን ሲሆን ብዙዎች ግን ዛሬም ዋነኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል የዘነጉበት ወቅት ነው።

ወደ አንድ ሀኪም ለምርመራ ሄደን በደስታና በእርካታ ሲመልሰን ወደ ሃኪሙ ተመልሰን የምንመጣበት ምክንያት የለም በማንኛውም ሁኔታ ህመም ከተሰማን የሃኪሙን የምርመራ ውጤት በናፍቆት እንጠብቃለን። ስለዚህ የሰው ዘርና የመላው ዓለም ፈጣሪ እግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ ላሉብን ችግሮች መፍትሔውን ከቃሉ ለማግኘት ጥረት እናድርግ። (2 ጢሞ. 3:16)

## ማለዳ በእግዚአብሔር ቃል እንሞላ

**(በአንድሪው ሙሬ)**

በማለዳ ጠዋት የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ትልቅና ልዩ ፀጋ ነው። በተቀረው የቀኑ ውሎአችን ሥራችን የሚባረከው ከፈተናና ከጥፋት የሚድነው የዕለቱን መጀመሪያ በቅዱስ ቃሉ ተሞልተን ስንሰማራ ነው።

በየቀኑ ለፀሎትና ለቃሉ የምናደርገው ዝግጅትና ተሳትፎ እንደግዴታ ከተቆጠረ ከዚያ ፀሎትና የቃሉ ንባብ ድካምና ሸክም የምናተርፍበት ብቻ ይሆናል። ሆኖም ግን በቅዱስ ቃሉ በተጻፈልን መሰረት የማለዳ ፀሎታችንና የቃሉ ጥናታችን በእግዚአብሔር

የዘለዓለም ሕይወትና የተስፋ ቃሎች መሰረት ካደረግን ውጤት ያለው ፍሬ ያለው የተትረፈረፈ በረከት የሚገኝበት ይሆናል።

በማለዳ ፀሎታችንና የቃሉ ጥናታችን የእግዚአብሔር መገኘት ዋነኛ አጀንዳችን መሆን አለበት። የፀሎትና የቃሉ ጊዜያችንም እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኘው መንፈስ ከተካሄደ ውጤቱ ያማረ ይሆናል።

የእግዚአብሔር መገኘትን ከሚከለክሉ ሀሳቦችና ነገሮች በፍፁም መራቅ ይኖርብናል። ከእግዚአብሔር ጋር በቃሉ በፀሎት ለመገናኘት የሚረዱ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. ከእግዚአብሔር የሚለዩ ሃሳቦችና ያልተናዘዝናቸው ኃጢያቶችን ሁሉ በንስኃ እናስወግድ፤

2ኛ. በመንፈስ ቅዱስ መረዳት እንጂ በራሳችን ጥበብና ማስተዋል ቃሉን ለመረዳት ፈፅሞ አንሞክር፤

3ኛ. ቃሉን በምናጠናበት ወቅት ወዲያውኑ ራሳችንን ለቃሉ ለመታዘዝ በእሺታ መንፈስ እንቀበለው፤

4ኛ. የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀትና ጉጉት እናንብበው። የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት ማጥናት የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለመረዳት ይጠቅማል፤ "የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን" (ቆላ. 1:9)

# የተገቢ ህይወት እድገት

በሩት ፓክሰን

"እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደመስታወት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።" (2 ቆሮ. 3:18)

በመንፈሳዊ ልምምድ የማያድግ እንቅስቃሴ የለም። የውስጥ ባርኮት በውጫዊ ገፅታ የሚገለፅ ጉዳይ ነው። በሚያድግ መንፈሳዊ ህይወት ከጌታ ጋር በሚኖር መጣበቅ እርሱን የመምሰል እድገት ይገኛል።

የክርስትና ህይወት እንደመልካም የወንዝ ጅረት ወይም ሐይቅ ነው። ጤናማ ተገቢ ህይወት ያለው ወንዝ በልምላሜ የሚያድግ ለሌላው መረስረስ የሚተባበር ሲሆን ህይወት የሌለው ወንዝ ግን የደረቀ፤ የዘቀጠ፤ ምንም አዲስ ፈሳሽ የማይገባበትና የማይወጣበት ይሆናል።

የክርስቲያን ህይወትም ከጌታ የተቀበልነውን ጤናማ መንፈስና ቃል ለሌሎች እያስተላለፈ ራሱም የለመለመ ሲሆን ለዚህ የተዘጋ ወንዝ ግን ህይወት አልባ ለሌላ የማይተርፍ የውድቀት ህይወት ክርስትና የተወ ሰው መለያ ነው።

የአማኞችና የክርስቶስ ማንነት የተመሳሰለ የሆነው ክርስቲያን በዚህ ምድር ኑሮው እግዚአብሔርን በመምሰል ከክፉ ስራዎችና ኃጢያት በመራቅ የሚኖር ከመሆኑ ላይ ነው።

በተጨማሪም የጤናማ ክርስቲያን ህይወት በሚገባ የሚያድግ ጤናማ አትክልትን ወይም ዛፍን ይመስላል። "ፍሬው የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል ... እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም።" (ዮሐ. 15፡2)

በክርስቶስ የሚኖሩት መልካም ፍሬ ይኖራቸዋል። ጌታም በቃሉ የሁሉንም ሰዎች በጎነትና ክፋነት በፍሬያቸው ታውቁዋቸዋላችሁ ብሏል። "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስንም መግዛት ነው። (ገላ. 5፡22)

እግዚአብሔር አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን ያብዛልን። አሜን

# እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን

**በጂ. ሲ. ራይል**

የእኔ ምኞት ሁሉም ሰው በእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ህብረት ውስጥ እንዲገኝ ነው። ሁሉም የክርስቶስ ማህበር ነኝ ወይም ቤተክርስቲያን የሚል ስም ያለው ሁሉ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ነኝ ይላል። ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ቤተክርስቲያን የሚታወቀው እንደ እግዚአብሔር ቃል ማህበረም ምእመናኑ ሲገኝ እንጅ ራስን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ብሎ መጠሪያ በመስጠትና እራስን በማስተዋወቅ አይደለም። እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኛት ዓለም ለማዳን ከሰማይ ሰማያት የወረደውን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምታምን ቃሉን የትጠብቅ ማህበር መሆኗ ነው።

እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ወይም ማህበረ ምዕመናን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ ብላ የምትመሰክር የምታምንና የምትቀበል ናት፤ "ጴጥሮስም መልሶ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔ ልጅ ነህ አለ ... ጌታም እኔም እልሃለሁ

አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እመሰርታለሁ" (ማቴ. 16፡18) እውነተኛዋ ማህበር ከሁሉም ነገድ ዘር ቋንቋ እና የህብረተሰብ ክፍሎች የተወጣጡ አባላት ያሉባት መሆኗን የጌታ መልዕክተኛ በዮሐንስ በራዕይ መፅሐፍ ላይ መስክሯል። "ከዚህ በኋላ አየሁ እነሆም አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከህዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ።" (ራዕይ 7፡9) ትክክለኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከውሃና ከመንፈስ እንደቃሉ የተወለዱ የሚገኝባት ሁሉንም ዘርና ቀለም የምታካትት እንጂ የአንድ ዘር ቀለም ወይም ቡድን ብቻ የያዘች አይደለችም።

እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባላቱ ፍፁም አንድነት ያለባት እርስበርሳቸው እንደ አንድ አካል ብልት የሚተሳሰቡ የተያያዙ ክፍሎች ድምር ውጤት ናት። (1 ቆሮንቶስ 12፡12) የቤተ ክርስቲያን አንድነትና ቅድስና ልክ በፍቅርና በቅድስና የተዋሀዱ ባልና ሚስትን ህይወት ይመስላል (ኤፌሶን 5፡27) የትክክለኛዋ በምድር ላይ ያለች የክርስቶስ አምባሳደር ወይም ተወካይ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል ያደርገን ዘንድ እንፀልይ እንትጋ።

## እግዚአብሔርን በሁሉም ሁኔታዎች ስለማመን

### በሚስዮናዊን አርተርና ዊልዳ ማቲዎስ

እግዚአብሔር አምላክን በሁሉም ሁኔታዎች በስደትና በመከራ በምቾትና በደስታ በጤንነት ጊዜ ወይም በህመም ወቅት አንድናምነው ጌታ ያስተምረናል።

ከክርስትና ጋር የሚቃረኑ ህይማኖቶችና ፍልስፍና ባሉባቸው የዓለም ክፍሎች ጌታን አምነው መከራውን ስለሚቀበሉ ወገኖች ልንፀልይላቸው ካለንም ልንረዳ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል።

‹‹ለቅዱሳን ስለሚሆነው አገልግሎት ልዕፍላቸው አያስፈልግምና በጎ ፈቃዳቸውን አውቃለሁና›› (2 ቆሮንቶስ 9፡1)

‹‹በመከራዬ ከእኔ ጋር ስለተካፈላችሁ መልካም አደረጋችሁ›› (ፊልጵሲዩስ 4፡14)

‹‹ እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉዋቸው ያደርጋችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና›› (ዕብራውያን 6፡10)

‹‹ለወንድሞች በምታደርገው ሁሉ የታመነ ስራ ትሠራለህ እነርሱም በማህበር ፊት ስለፍቅርህ መስክረዋል››

ለእግዚአብሔር እንደሚገባ አድርገህ በጉዟቸው ብትረዳ መልካም ታደርጋለህ››

(3ኛ ዮሐንስ መልዕክት) በዚህ ዘመን በእምነታቸው ምክንያት ከትውልድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጀምሮ በልዩ ልዩ የክፋት ሀይሎች ለሚፈናቀሉ፣ ለሚሰደዱ አልፎ አልፎ ለሚደበደቡና የግድያ ዛቻ ለሚደርስባቸው በተቻለን አቅም በፀሎት በገንዘብ በቁሳቁስ ልንደግፍ ያስፈልጋል።

በክርስትና ታሪክ የጌታ ደቀመዛሙርትና ሐዋርያቱ ብዙ በተሰደዱ ቁጥር በጣም እየበዙ ሀገሩን ሁሉ እየወረሱ ለዚህ ዘመን ደርሰናል። ከእውነተኛ እምነት የተነሳ የሚደርስ መከራና ስደት ክርስትናን ያጠራል፣ ብርታትንና በጌታ መታመንን ይሰጣል። "የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ" (ሐዋ. 8፡4)

ጌታ እግዚአብሔር በዚያ ክፉ ዘመን ዛሬም በሚገጥመን መከራ የሚደርስልን የተመሰገነ ይሁን!

# የግል ተሃድሶ

(በሮበርት ማክቼይን)

በክርስትና ገብ ለቤተክርስቲያንም ሆነ ለሀገር መንፈሳዊ እድገት ይገኝ ዘንድ መነሻው በግለሰብ ደረጃ አስቀድሞ ራስን በመመርመር በንስሃና ተሀድሶ መስተካከል ማድረግ ነው።

በቤተክርስቲያን ታሪክ በቅዱስ መፅሐፉም የተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሰዎች ለቤተክርስቲያንና ለሀገር ከዚያም ለዓለም መታደስ መፈወስና መነቃቃት ምክንያት የሆኑት ከግል ንስኃና ወደ እግዚአብሔር መመለስ በመጀመር ነው። "የሌዊንም ልጆች ይጠራል እንደ ወርቅና እንደ ብርም ያነጥራቸዋል።" (ሚክ.. 3፡3)

ከአስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች የሌዊ ነገዶች ከአባታቸው የተሰጣቸው ርስት መሬት ሳይሆን ከጌታ ቤት አገልግሎታቸው አስራት በኩር ነበር። በዚህም አገልግሎታቸው ለእግዚአብሔር ቤት ኃላፊነት ይበቁ ዘንድ መጥራት መንፃት መስተካከል እንደሚገባቸው በዚህ የትንቢት ቃል ተነግሯል።

በአዲስ ኪዳን ግን ሁሉም የክርስቶስ ተከታይ የክርስቶስ ካህን በመሆኑ በግል እራሱን ሊቀድስ ሊያነፃና ሊያጠራ ይገባል። ይህ መንፃት መጥራት የሚገኘውም በእውነተኛ ንስኃ በመስተካከል ነው።

በአዲስ ኪዳን የአማኞች አገልግሎት የተሟላና የተሳካ የሚሆነው በእምነት የዓለምን የክፉ ሰይጣንን አሰራር በማሸነፉ ስጋንም በመጎሰም በቅድስና ኑሮ ነው። "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና።" (1 ዮሐ. 5፡4)

በግል ተሃድሶ ጌታን ማገልገልና ማስደሰት ለራስም ሆነ ለሌሎች በረከት የሚኾነው ራስን ሙሉ በሙሉ ለጌታ በመስጠት ነው።

በግማሽ ልብ ጌታን በግማሽ ልብ ዓለምን እያገለገሉ የጌታን ፍሬዎች በህይወታችንና በሌሎች ማስገኘት ፈፅሞ አይቻልም።

"ከደበቁብኝ ወጥመድ አውጣኝ በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ የእውነት አምላክ ተቤዠኸኝ" (መዝ. 31:5)

እራሳችንን በማጥራት፣ በማንፃትና በመቀደስ ሌሎቹን ለመቀደስ ጌታ ያብቃን።

## ልጆቻችንን በጌታ ስለማሳደግ

(በኪም ቡትስ ፤የአሜሪካ የፀሎት ህብረት)

በልጆች ላይ የምናውለው መንፈሳዊ ስራዎች የሀገርና የቤተሰብን ቀጣይ ክርስቲያናዊ ኑሮ የሚወስን ይሆናል።

የክርስቲያናዊ ልጆች አስተዳደግ ምሳሌ እራሱ የክርስትና ጀማሪና ፈፃሚ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።" (ሉቃስ 2:52) በእግዚአብሔር ፊት ልጆቻችን ያድጉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃልና ፀጋውን እንደጌታና እንደ እናቱ ቅድስት ማርያም ዘመድ መጥምቁ ዮሐንስ ከማህፀን ጀምሮ ይካሄዳል።

በእግዚአብሔር ፊት ልጆች እንዲያድጉ የእግዚአብሔር ቤት ቅን አባላት መሪዎችና አገልጋዮች ተዋፅኦ እጅግ ተፈላጊ ነው።

ፍቅር በሌለበትና በግብዝነት በፉክክር በዓለማዊ ድርጊት በተሞላ ቤተሰብና ማህበረሰብ ያደጉ ልጆች የብዙ ጥፋቶች ተዋናይ ናቸው። በሌላው በኩል በወላጆቻቸውና በቤተክርስቲያን አገልጋዮች ደግነትና ፍቅር ያደጉ ለብዙ ትልልቅ ሀገራዊና ማህበራዊ ከዚያም አልፎ ዓለም አቀፋዊ መልካም ስራዎች መንፈሳዊ መነቃቃት ምክንያትና ተባባሪ ይሆናሉ።

በልጆች ፊት ማንኛውንም ውሸት ስልክ ሲደወል የለም ብሎ እንዲመልሱ ከማስዋሸት ጀምሮ ልጆችን የሚጎዳ ተግባር ኃጢያት ነውና ማናቸውንም ጥፋትና ኃጢያትን ላለመስራት እንጠንቀቅ። ሰው በመሆናችን ስናጠፋና ኃጢያት ስንሰራ ደግሞ ህስኃ መግባታችን ይቅርታ መጠየቃችን በልጆቻችን ፊት የታወቀ መሆኑ ትልቅ ትምህርት ሰጭ ነው። "ኃጢያታችን ብንናዘዝ ኃጢያታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነ ፃድቅ ነው። ኃጢያትን አላደረግንም ብንል ሀሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።" (1 ዮሐ. 1:8) ልጆቻችንን የሚመሰክሩ የእግዚአብሔርን የሚፈልጉ ለማድረግ በፀሎት እንጋደል።

# መልዕክት ከአማርኛው ትርጉም አቀናባሪ

(ኤዲ (አደፍርስ) ሀብቱ መካሻ)

“ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ ፈጣሪ ትዘረጋለች” (መዝ. 67፡31) ሀገራችን ኢትዮጵያ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ በብዛት ከተጠቀሱት ጥቂት ሀገሮች ውስጥ አንዷ ስትሆን በአሞፅ ትንቢት ላይ ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ መወደሷን የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል።

ክርስትናን ከተቀበሉት ቀዳሚ የሰው ዘር መገኛ ሥፍራ መሆኗን መፅሐፍ ቅዱስም ሆነ የሰው ዘር የታሪክ ምርምር ያረጋግጣሉ።

ሆኖም ግን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከታሪክ አንጋፋነት ባልዘለለ በመንፈሳዊ እድገትና በሰላም ከዓለም ሀገራት በመጨረሻዎቹ ደረጃ ላይ መሆኗን መካድ አይቻልም።

በቅርብ ዘመናት በሀገራችን ኢትዮጵያ የተከሰቱ ረሀብ ጦርነት የኮቪድ ወረርሽኝ በሽታ በሰሜኑ ክፍል የተካሄደ ወደ መሀል ሀገር ዘልቆ የነበረው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የታየው የዘር ጥላቻና እልቂት በድህነታችን ላይ ከፍተኛ ተጨማሪ ጉዳት አድርሶብናል።

የዛሬው ክርስትና /Christianity today የሚባለው የወንጌላውያን መፅሔት የ2021 እትም በአማኞች መካከል በርስ በርሱ ጦርነት የተነሳ የተከሰተውን አስቀያሚና አስፀያፊ መከፋፈል መደበቅ አይቻልም።

በወንጌል ሥራ በሚሰሯን አገልግሎት ቀዳሚ ነን ባሉት የምዕራብና የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍሎች የታየው ዘር ተኮር ጭፍጨፋ ማፈናቀል ከዚያ የተወለዱት የወንጌል አገልጋዮች በሚያስተዳድሩት ሚድያና ማህበራዊ ሚዲያ ሳይቀር የመሰከሩት ነው።

ይህን ሁሉ እያየንና እየተመለከትን እንደ እግዚአብሄር ሰው በጾም ፀሎት ከመትጋት ይልቅ የአንዱ ወገን ተዋጊ ደጋፊ የሌላው ወገን አጥቂ ተባባሪ ሆነን በመገኘታችን በጊዜው ንስኃ ልንገባ ይገባል።

በዚህ አስከፊ የሰቆቃ ዘመን በእራስ ወዳድነት ጆሯችንን የደፈንን ወይም የወገኖቻችንን ስቃይ ረስተን ለግል ኑሯችን መሻሻል ሁኔታዎቹን የተጠቀምን እንዲሁ ተገቢ ንስሃ እንግባ።

ጥቂቶች ከማንም ሳይወግኑ በብዙ እምባና በፀሎት ለሀገራችን ኢትዮጵያ ምልጃና ፀሎት ያቀረቡት ጌታ ሰምቶ ጦርነቱ ባይቆምም ወራሪዎቹ ከወረሩት ሥፍራ ቢወጡም ዛሬም ነገም የዚህ ስቃይና ግፍ ሰለባዎች ታሪክና የወደፊት ቀጣይ ቁምና የበቀል መንፈስ በሀገራዊ ይቅርታና ንስኃ ሊዘጋና አዲስ ምዕራፍ ሊጀምር ይገባል። የዚህ ዓይነቱ በዘርና በፖለቲካ ልዩነት የተፈጠረ

ሀገራዊ ቀውስ ሃያ ሰባት ዓመት ጥላቻ ሲሰበክበት ቆይቶ መራራ ፍሬው በመታየት ላይ ነው።

የቀደመው የደርግ ወታደራዊ መንግስት በተወገደበት ሰሞን የግዮን ሆቴል በ1984 ዓ.ም ሀገራዊ የእርቅና የሰላም ኮንፍረንስ እንዲደረግ እጅግ የተጉ ዛሬ በአካል በህይወት የሌሉ እንደነበሩ በዚያን ወቅት መሪዎች ከነበሩት ሰው ተርጓሚው ማረጋገጫ አግኝቻለሁ።

ስለዚህ የወንጌል አማኞች ሁሉ ሌሎቹም ክርስቲያኖች ለሀገራችን ኢትዮጵያ የእርቅና ሰላም የይቅርታ ጉባኤ ይጠሩና ይተባበሩ ዘንድ በጌታ ፍቅር እጠይቃለሁ። "በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው በፀልዩ ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ኃጢያታቸውን ይቅር እላለሁ ምድራቸውን እፈውሳለሁ።" (2 ዜና 7:14)

# ዓለም አቀፍ የፀሎትና ምስጋና ርዕሶች

## ለሄይቲ የከፋ ቀውስ እንፀልይ

በሄይቲ ባለው ከፍተኛ የፖለቲካ ግጭትና በውጭ መንግስታት ጫና ለተጎዳውና ለታወከው ሕዝብ በብርቱ እንፀልይ።

የሄይቲ ነፃነት መሪ ማርክ ጋርቬስ "ወደ አፍሪካ እንመለስ" ጥያቄ ትግል እንዲጀመር ያሳሰበ ነበር። ሄይቲ የውጭ ወራሪ ኃያላንን ድል ስታደርግ ተባብረው ነፃነቷን የገፈፉባት ሃገር ስትሆን የአፍሪካና የጥቁርነት ስሜታቸው እጅግ ከፍተኛና ልዩ ነው።

## የውርጃን መንፈስ በፀሎት እንመክት

ያልተወለዱ ህፃናትን የማጥፋት ኃጢያት እየተባባሰ ይገኛል። ይህንን እጅግ ብዙ ሚሊዮን ህፃናትን የሚገድል እርም በፀሎት እንፋለም።

## ለአፍጋን ስደተኞች ፀሎት

በታሊባን አመፀኞች የተነሳ የተሰደዱ የአፍጋን ዜጎችን በፀሎት እናስባቸው። በየሄዱበት ሀገር ጌታን እንዲቀበሉት ጥረቱን በፀሎት እንደግፍ።

## ለእስራኤል እንፀለይ

የብሉይም ሆነ የሀዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ ምሳሌ ሆና የቀረበች ይሁዲ እስራኤልን በጸሎት እናስባት።

## ለኢትዮጵያ ይቅርታና ምህረት ፀሎት

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከ30 ዓመታት በፊት በቤተ እምነቶችና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ተጀምሮ የነበረው የሀገራዊ ይቅርታና እርቅ ጉባኤ ይሳካ ዘንድ እንፀልይ።

በቅርቡ በተካሄደውና ላሬም በተለያዩ ስፍራዎች አልፎ አልፎ የሚካሄደው የዘር ተኮር ጥቃትና ወረራ ይቆም ዘንድ በፀሎት እንበርታ።

**ለተሰደዱ ክርስቲያኖች እንፀልይ**

በእምነታቸው ምክንያት በዓለም ዙሪያ ለተሰደዱና ለሚሰቃዩ አማኞች ያላቋረጠ ጸሎት እናድርግ።

**ለየምዕዓቱ የምስራች እንማልድ**

የወንጌል መነቃቃትና ተሀድሶን ትምህርቶች በተለያዩ ቋንቋዎች የሚያሳትመውና የሚያሰራጨውን ይህን አገልግሎት በፀሎት እንተባበር።

**ለሚሲዮን ሥራዎች እንፀልይ**

በዓለም ዙሪያ ነፍስንም ስጋንም የሚያድነውን መልዕክት ለሚያሰራጩና ለሚያሳትሙ የምዕአቱ የምስራች አገልጋዮች ብርቱ ፀሎት እናድርግ።

# የተስፋችን ትልቁ ምክንያት

**(በአስቲን ስፓርክስ)**

**“በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ግን ይቻላል።” (ሉቃ. 18:27)**

በክርስትና እምነት ላሬና ጠቅላላው መጪ ጊዜ በትልቅ ተስፋ የሚጠበቅ ነው። “ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ።” ያለን የትንሳኤው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠን ተስፋ መሰረት ለዚህ ተስፋ ትልቁ ምክንያት ሆኗል።

በእግዚአብሔር ያለን ተስፋ ትልቅ የመሆኑ ምክንያቶች ማረጋገጫው አንዳንዶች ሊተቹት የሚፈልጉት በቅዱስ ቃሉ የተገባልን በራሳችን የማንችለው አንዳች እቅድ ሃሳብ ወይም ስራና ትዳር ቢሆን እኛ ምንም የማንችለው ቢሆንም ሁሉን የሚችለው እግዚአብሔርን ማሳወቅ ነው። ጌታ በቃሉ ሐዋርያው ጳውሎስ በአንዳንድ ጉዳዮች ተስፋ እንዳንቆርጥ የሚሠጠን ምልክት የታመነ ነው። ‹‹ድንጋዩ ይበቃሃል ኃይሌ በድካም ይፈፀማል›› (2 ቆሮንቶስ 12:9) ሌላው የተስፋችን ትልቅ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ሰው ሆኖ የተወለደው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ነው።

‹‹ሀይልን በሚሠጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ›› (ፊልጵስዩስ 4:13) በክርስትና እምነት በብርቱ ተስፋ በምንታመንባቸው የእግዚአብሔር በረከቶች አያሌ ትምህርቶች በቅዱስ መፅሐፍና በአያሌ መፀሐፍቶቻችን ላይ ይገኛሉ።

በብሉይ ኪዳን የተነገረለት በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ እለት የተወለደው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እሰከለዘላለም የማይለወጥ

ሕያው ተስፋችን መሆኑን ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጣል።

‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም እስከ ለዘላለም ያው ነው›› (ዕብራውያን 13፡8)

የዘላለም ህይወት እንዳለን የአማኞች ማረጋገጫ የተስፋችን ትልቁ ምክንያት ሞትን ያሸነፈው ከሞት የተነሣውና ወደሰማይ ያረገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የጌታን ትንሣኤ ለማስካድ ያኔ የነበሩት ግብዝ የሃይማኖት መሪዎች ገቦ ሠጥተው እንዲወራ ሲያደርጉ ዛሬም ደን ብራውንና መሳዮቹ ጌታን ስጋዊ ሰው ብቻ በማድረግ ቢጽፉና ቢያስቱም ምንም ማስረጃና አንድም እውነት አልተገኘባቸውም። ምክንያቱም እንደተፃፈው እርሱ መበስበስን አላየም። ሞትን በትንሳኤ አሸንፏልና። ሃሌሉያ!

# የእግዚአብሔር ሰራተኞች

በዴቪድ ትራየን

በቅዱሱ መፅሐፍ እኛ ስጋ ለባሽ ሰዎች የቅዱሱና የዘለዓለማዊው አምላክ የስራ ተባባሪዎችና ባልደረቦች ተብለናል። ‹‹ከእርሱ (እግዚአብሔር) ጋር የምንሠራ ነንና›› (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡9)

ከእግዚአብሔር ጋር የምንሠራ ነን ብሎ ቅዱስ መፅሐፍ የሚያስተምረን ከእግዚአብሔር የማዳን ስራ የሰው አስተዋፅኦ አለበት ለማለት ሳይሆን በእግዚአብሔር ልጅነት የእግዚአብሔር ማዳን ፈውስና በረከት በእኛ አገልግሎት ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስና ሠራተኛነት ይፈፀማል ለማለት ነው።

የእግዚአብሔር ስራ በእኛ ውስጥ ማለፉና እኛን የእግዚአብሔር ሠራተኞች የሚያደርገን እያንዳንዱን የእምነት ስራና የእግዚአብሔር ቃል የማስፋፋት ስራዎችን በጌታ እየተሰራ በመጨረሻው ፍሬው ስለሚታይ ነው። ‹‹በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግስት እንደዚህ ናት፣ ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሳልም ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪ ቡቃያ ከዚያም ዘር ኃላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች›› (ማርቆስ 4፡26) የእግዚአብሔር ስራና የነፍሳት አዝመራ በትንሽ ይጀምርና እያደገ እየሰፋ ምድርን ሁሉ ይወርሳል፣ ‹‹በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻ›› (ሐዋርያት 1፡8)

የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ታታሪ የእምነት ስራ ባልደረቦች ሁል ጊዜ በእምነት የሚካሄድና የእግዚአብሔር መንግስት ስራ

ከእምነቱ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ በሚፈጥረው ፀጋ በእምነት መፈፀሙ ነው።

የእምነት ስራዎች በቅዱስ መፅሐፍ የተጠቀሱት ጌታ ለሚሠራቸው ሥራዎች ሁሉ ማዕከሉ እምነት ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በመረዳት እንትጋ። ይህ የእግዚአብሔር የፀጋ ሥራ እንጂ የሥጋ ለባሽ የእምነት ሰው ሥራ አይደለም። "ፀጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም"። (ኤፌ. 2:8)

በፀጋው የእምነት ሥራውን በእኛ ውስጥ ያብዛልን!

## የእግዚአብሔር ቃል ስውር መሣሪያና እሳት ነው

የ18ኛውና የ19ኛው ክፍለ ዘመናት ታላላቅ መንፈሳዊ መነቃቃቶችና የእግዚሐአብሔር ገብኝትቶች መሣሪያ የሆኑት የሞራቪያን አገልጋዮች ድንቅ ሥራ የተጀመረው እንደ እሳት የሚቀጣጠል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነበረ።

በ1796 ዓ.ም በጀር መናዊው የሞራቪያን አገልጋይ የተሰጠው እሳት ቀስቃሽ አገልግሎት መሪ ጥቅስ "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊያድን መጣ" በሚለው ሉቃስ 19:10 መነሻነት ነው።

ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መነካት መጥፋቱን ከጌታ መለየቱን በቃሉ አምኖ ሳይቀበል አንዳች የመንፈስ ቅዱስና የወንጌል ሥራ ሊካሄድ አይችልም።

የሞራቪያሬያን ሰባክ. ቃላት ልቧ የደነደነ ሴትን ህይወት ለመለወጥና ለሌሎች እንድትመሰክር ሊያበቃ በዚያ አስደናቂ ለውጥና ምስክርነት አያሌዎች እየተነሱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደ እሳት መቀጣጠሉን ተያያዘው።

ከዚያ መልዕክት የተነሳ ብዙዎች ተነስተው አስደናቂ የሚሲዮን ሥራ ወንጌልን በብዙ የአለም ክፍሎች ማዳረሱ በስፋት ቀጠለ።

የእንቅስቃሴውም ስም ሳብራደር ጴንጠቆስጤ ተብሎ በኤርሚያስ 23:29 መሠረት የበለጠ ተስፋፋ። "በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፤ ድንጋይንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደለችምን"

የእግዚአብሔርን ቃል በምንሰማበት ጊዜ ወደ ልባችን ገብቶ የሚገጥመንን የሰይጣን ጥቃት ይከላከልልናል። "አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ" መዝ 119:11። ለኮቪድም ሆነ ለሌሎች በሽታዎች የምንከተበው መድኃኒት በውስጣችን እንደሚከማች ታላቁ ፈዋሽ የጌታ ቃል እንዲገኝብን በብርቱ ፀሎት ቃሉን እንመገብ! "ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ህግ ይሻለኛል" መዝ 119:72

# የአንባቢያን ደብዳቤዎች

## ከእንግሊዝ

የምጽአቱ የምሥራቹን ብዙ በመከታተሌ ትልቅ መንፈሳዊ ጥቅሞችን አግኝቻለሁ።

የጌታችን ዳግም ምጽአት እንዳስብ ረድቶኛል። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

## ከዩጋንዳ

የምጽአቱ የምስራችን ለአመታት በመጠቀሜ በቻፕሊያን አገልግሎቱ ብዙ ተጠቅሜበታለሁ። በወቅታዊ መልዕክቶቹ ብዙ ታንፀንበታል።

## ከዛምቢያ

እግዚአብሔርን ስለምጽአቱ የምስራች እጅግ አመሰግናለሁ። አገልጋዩቹንም ጌታ ይባርካችሁ።

## ከጉያና

ይህን ደብዳቤ የምጽፍላችሁ የሐምሌና የነሐሴ እትሞች እንደባረኩኝ ሲሆን ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ የጋዜጣችሁ ተከታታይ ነኝ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

## ከአውስትራሊያ

ለዓመታት በታማኝነት ለምትልኩልኝ የምጽአቱ የምስራች ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ። ለታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት እየፀለይን ነው። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

## ከራሽያ

የምጽአቱ የምስራችን ለዘመናት በማንበብ ላይ ነኝ። ጋዜጣችሁን ደጋግሜ በማንበብ ብዙ ምክሮችን አግኝቼበታለሁ።

## ከኢትዮጵያ

በየምጽአቱ የምስራችን እጅግ ተባርኬአለሁ። በሀገራችን በተፈጠረው ሁኔታ ባዝንም በእግዚአብሔር ቃልና በጋዜጣችሁ ተጽናንቻለሁ።

## ከአሃዮ

አንድ ሰው የምጽአቱ የምስራች ጋዜጣን አውሶኝ እጅግ ተባርኬባታለሁና በአድራሻዬ በመላክ ተባበሩኝ።

## ከኒውዮርክ

መንፈስን ስለሚያነቃቃው ጋዜጣችሁ ልባዊ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ። ጋዜጣችሁን ባነበብኩ ቁጥር በመንፈስ እሞላለሁ።

## ከቴነሲ

የምጽአቱ የምስራች ወንጌል ለሁሉ እንዲዳረስ የሚያደርገውን ትጋትና ጥረት እናደንቃለን። መልካሙን ገድል በዚህ አገልግሎት በጋራ እንፈጽም ማራናታ!

# ልዩ የቸርነት ማስታወቂያና የእርቅ ጥሪ

## ለተፈናቀሉት የእርዳታ ጥያቄ

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተፈጠረው የእርስ በርስ ጦርነትና ኢፍትሐዊ ወረራ የተጐዱትን በፀሎትና በምክር ከቻልንም በገንዘብና በቁሳቁስ እንርዳ።

በተቻለ መጠን ዘርን ከዘር የሚያጋጭ ንግግር እናቁም። ክፉ መንፈስን እንቃወም በጾምና ፀሎት እንትጋ ይቅርታን እንስበክ።

በድህነታችን ላይ ጦርነቱ ባስከተለው ጉዳት እጅግ በጣም የተጠቁ በአማራ፣ በአፋርና በትግራይ ክልሎች ለሚገኙ ወገኖቻችን እርዳታ ለሚያደርጉ ትብብር እናድርግ። እንደገና ወደዚህ መሰለ መተላለቅ እንዳንገባ የእምነት ሰዎች ብርቱ ፀሎትና ትምህርት እናስፋፋ ደም ማፍሰስን የሚዘራውን ሠይጣንና ክፉ መላዕክቱን በብርቱ ፀሎት እንዋጋ።

ለተገኘው ሰላም ለጌታ ምስጋና እናቅርብ ይቅርታንና ምህረትን እንስበክ።

## የመዳን መክሮች

ከሚመጣው ቁጣ ለመዳን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሚከተሉትን ምክሮች እንከተላቸው።

1. የእግዚአብሔርን ቃል ከልብ በማንበብ ሁላችንም ከአዳም ዘር የተወለድን ኃጢያተኝነታችንን እንወቅ፣ ዘፍጥረት 3:7 ሮሜ 3:23
2. ንሰሀ ገብተን ወደሚቀርበን ቤተክርስቲያን እንሂድ፣ ሮሜ 6:23 ሮሜ 10:9፣ የሐዋርያት ሥራ 2:38

## የምጽአቱ የምስራች የአንባቢዎች መዋጮ

ይህንን ጠቃሚ የትርጉም ሥራ ተርጓሚው በነፃ በመተርጐም በራሴ ወጪ ታይፕ በማሰራት ወደ አሜርካ እልካለሁ። ይህንን ሀገር ቤት የምታስተባብር እህታችን አልማዝ አሳየ በፓሣቱ 8986 አዲስ አባባ ጌታ ያሳሰባችሁን ላኩላት በፀሎትም ደግፏት።

## በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው (ራዕይ 14:13)

ባለፈው 2013 ዓ.ም የምጽአቱ የምሥራች ሁለት አገልጋዮች ወደ ጌታ እቅፍ ገብተዋል። አቶ አማረ ማሞ የመጀመሪያዎቹን እትሞች አርትኦት በመሥራት የተባበሩንና በአገልግሎቱ ህብረት ታታሪና ታማኝ አገልጋይ ወ/ሮ ሠፋኒት አክሊሉን በስጋ ብንለይም ወደ ጌታ ክብር በመግባታቸው እንጽናናለን። ለእነዚህ ወገኖች ቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ የመጽናናት ጸሎታችሁን እንጠይቃለን።

*የምጽአቱ የምስራች ወንጌል አገልግሎት (ስልክ 0912120402)* ፓሣቱ 8986 አዲስ አባባ